BELLWETHER
HOUSING

Amharic/አማርኛ

ግንቦት 7 ቀን 2025

ርዕሰ ጉዳይ፡ ወደ Kingway ምዕራፍ 1 የመልሶ ማልማት መርሃ ግብር መዘግየት

ውድ የ Kingway ነዋሪዎች፣

ይህ ደብዳቤ በ Kingway Apartments ውስጥያሉትን ሕንፃዎች የመተካት ዕቅዳችን መዘግየቱን ለማሳወቅ ነው። ለዚህም ምክንያቱ አሁን ሕንፃዎቹን ለመተካት የሚያስችል የገንዘብ ድጋፍ ስለሌለን ነው። አሁንም የገንዘብ ድጋፍ ሲኖር ህንፃዎቹን ለመተካት እያቀድን ስንሆን፣ አዲስ መረጃ እንደደረሰን እናሳውቆታለን። አዲሱ መርሐ ግብር እንደሚከተለው ይሆናል፡-
በ A፣ B፣ C፣ D፣ E፣ F፣ G፣ H፣ M፣ N፣ P እና Q ሕንፃዎች ውስጥ የሚሆነው ይህ ነው፡-
በጁን 2028 A፣ B፣ C፣ D፣ E፣ F፣ G፣ H፣ M፣ N፣ P፣ እና Q ህንፃዎችን እንዘጋለን ብለን እንጠብቃለን። አዲሶቹ ህንጻዎች በጁላይ 2030
ሲጠናቀቁ የማጣሪያ መስፈርቱን እና የገቢ መመዘኛዎችን ካሟሉ ወደ እነርሱ ለመግባት ቅድሚያ እድል ይኖርዎታል።

ከ2027 ክረምት ጀምሮ፣ በእነዚህ ህንፃዎች ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ፣ የ Bellwether ማዛወሪያ ቡድን አባል የቤተሰብዎን ልዩ ፍላጎቶች እና ምርጫዎች ለመረዳት ከእርስዎ ጋር በመገናኘት አዲስ ተመጣጣኝ ቤት እንዲያገኙ ያግዝዎታል። እንዲዘዋወሩ ሲጠየቁ Bellwether ወደ አዲስ ቦታ ለመዘዋወሪያዎ በመክፈል ይረዳዎታል። ከዚህ ጊዜ በፊት ወደ አዲስ ቦታ ለመዛወር ከመረጡ Bellwether የመዘዋወሪያዎን ክፍያ አይረዳዎትም።
ይህ የጊዜ ሰሌዳ በገንዘብ አቅርቦት ላይ ተመስርቶ ሊዘገይ ቢችልም፣ ቀደም ብሎ አይከናወንም።በጊዜ ሰሌዳው ላይ ስላሉ ለውጦች በተቻለ ፍጥነት እናሳውቆታለን።
በ I፣ J፣ K፣ L፣ R፣ S እና T ሕንፃዎች ላይ የሚሆነው ይህ ነው።
እነዚህ ሕንፃዎች ቢያንስ ለ5 ዓመታት ተጽዕኖ አይኖርባቸውም። አንዴ የእነዚህ ሕንፃዎች እቅዳችን ግልጽ እንደሆነ፣ እናሳውቅዎታለን።

እንደ Kingway ነዋሪ ለእርስዎ አክብሮት አለን። እንደዚህ አይነት ለውጦች አሳሳቢ ሊሆኑ እንደሚችሉ እናውቃለን፣ ስለሆነም እርስዎ እና ቤተሰብዎ ወደ አዲስ ቤት እንዲገቡ እና እንደተጠናቀቀ ወደ አዲሱ እና የተሻሻለው የ Kingway Apartments እንዲመለሱ ለመርዳት

የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን።
ይህ መረጃ ከተቀየረ እናሳውቆታለን። አመሰግናለሁ፣

Jovan Ludovice
የሪል እስቴት ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት
የ Bellwether Housing

የግንኙነት መንገድ፥ kingway_redevelopment@bellwetherhousing.org
ድረ ገጽ: https://www.bellwetherhousing.org/properties/kingway-redevelopment